በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /??? 203214
?? 29/3/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - የጉምሩክ ኮምሽን - የቀረበ የለም

ተጠሪ - አቶ ተስፋ ዮሀንስ - ጠበቃ ካላአዩ አያለው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች የካቲት 19 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 195827 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 243070 ሐምሌ 3 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 ተገቢ ያልሆነ ትርጉም በመስጠት የተሰረዘ ዲክላራሲዮን ጸንቶ ያለ ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 የእቃ ዲክላራሲዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ 5 የሥራ ቀን ድረስ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ካልጀመረ ዲክላራሲዮኑ ሊሰረዝ ይችላል እያለና በተጨማሪም የደንብ ቁጥር 118/08 አንቀጽ 20(1) ሊሰረዝ እንደሚችል ደንግጎ እያለ ላይሰረዝ ይችላል የሚል ትርጉም መስጠቱ ካለአግባብ ሲሆን ግመሎቹ ከህጋዊ መስመር ውጪ ወደ ሱዳን ለመግባት ሲሉ መያዛቸው እየታወቀ ጊዜ ባለፈበት ዲክላራሲዮን ህጋዊ እንደሆኑ ተወስዶ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ታክስ ይግባኝ ኮምሽን ሲሆን ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የአሁን ተጠሪ የቁም እንሰሳት ወደ ውጪ የመላክ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡ 43 ግመሎች ወደ ውጪ ለመላክ በ7/12/2008 ዓ/ም እና በ13/12/2007 ዓ/ም ህጋዊ ዲክላራሲዮን የተመታለት እና በቀን 22/11/1007 ዓ/ም እቃ ወደ ውጪ መላኪያ የባንክ ፈቃድ ተሰጥቶኛል፡፡ በወቅቱ በሱዳን መንግስት የቁም እንሰሳት ወደ ሀገር እንዳይገባ በመከልከሉ የዘገዩና በፌደራል ፖሊስ ጥበቃ ስር ከቆዩ በኋላ በራሴ ጠባቅዎች እያስጠበኩ ባለሁበት ሁኔታ 5 ቀን ያለፈበት ዲክላራሲዮን ነው በሚል እግራቸው ታስሮ ተኝተው እያሉ ግመሎቹ በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሱዳን ሊሻገሩ ነው በሚል መውረሱ ተገቢ ባለመሆኑ ይለቀቅልኝ ሲል አመልክቷል፡፡ የአሁን አመልካችም ግመሎቹ የይግባኝ ባይ አለመሆናቸው ለዚህም ደግሞ በወቅቱ መቅረጫ ጣቢያው ዲክላራሲዮኑ ሲሰረዝ በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ሥር ከሚገኙ ግመሎች መካከል የይግባኝ ባይ ግመሎች የሚገኙ እንደሆኑ ለማጣራት በአካል ቀርቦ እንዲለያቸው ቢጠየቅ በማፈግፈግ መብቱን አልተጠቀመም፡፡ በተደረገው የመስክ ምልከታም የይግባኝ ባይ ግመሎች እንዳልተገኙ አረጋግጠናል፡፡ በተጨማሪም ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ 5 የስራ ቀናት ያለፈበትና ቀጣዩ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት ያልተጀመረበት በመሆኑ ይግባኝ ባይ ህጋዊ ዲክላራሲዮን አለው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው ይጽናልኝ በሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ታክስ ይግባኝ ኮምሽን አከራክሮ በመ/ቁጥር ታይኮ ከተ-1642 ሴኔ 3 ቀን 2011 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 መሰረት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክላራሲዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማሳወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ 5 የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት ካልተጀመረ ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል ሲል ይደነግጋል፡፡ በመመሪያ ቁጥር 118/08 አንቀጽ 20(4 እና 5) እቃ ወደ ሀገር እንዲገባ ወይም እንዲወጣ ከተፈቀደ ቀን ጀምሮ በተለያየ ምክንያት ሳይፈጸም ከቀረ በ10 ቀናት ውስጥ ሲያሳውቅ ሊሰረዝ እንደሚችል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም ከዚህ በላይ ከቆየ በበቂ ምክንያት እስከ 1 ዓመት በሆነ ጊዜ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ ዲክላራሲዮኑ እንደሚሰረዝ ይገልጻል፡፡ ይሁንና ቀርቦ ያላሰረዘ እንደሆነ መብቱ የሚቀር ይሆናል፡፡ በመሆኑም ግመሎቹ ዲክላራሲዮን ተሰጥቶበት ወደ ውጪ ሳይወጡ የቀሩና መልስ ሰጪም የሚያውቅ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ዲክላራሲዮን መሰረዝ የመ/ሰጪ መብት ሲሆን እያወቀ መቆየቱ ተገቢ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ይ/ባይ ግመሎቹ ወደ ውጪ መውጣት የማይችሉ ከሆነ ዲክላራሲዮን አሰርዞ ከጉምሩክ ክልሉ ማውጣት ሲኖርበት መ/ሰጪም ከጉምሩክ ክልሉ እንዲወጡ ማስገንዘብ ሲገባ በዝምታ መታለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይ/ባይ ጊዜ ያለፈበት ዲክላራሲዮንና ግመሎቹ ወደ ውጪ መውጣት የማይችሉ መሆኑን እያወቀ ዲክላራሲዮን ማሰረዝ ስገባው በጉምሩክ ክልል ውስጥ ማቆየቱ ተገቢ ባለመሆኑ መወረሱ ስህተት አይደለም ሲል የመ/ሰጪን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ባይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ አከራክሮ በመ/ቁጥር 243070 ሐምሌ 3 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ባይ በህጋዊ መንገድ 43 ግመሎች ወደ ውጪ ለመላክ በመ/ሰጪ ፈቃድ በድንበር ላይ የተገኘ መሆኑ የተረጋገጠና ባልተወቀ ሁኔታ ወደ ውጪ ሳይላኩ የቆዩና የይግባኝ ባይ ዲክላራሲዮን 5 ቀን ያለፈበት መሆኑ ታውቋል፡፡ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15(1) እቃ ወደ ወጪ ሳይላክ የቀረና በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ቀጣይ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት ካልጀመረ ዲክላራሲዮኑ ሊሰረዝ እንደሚችል ይገልጻል፡፡ ካልተሰረዘ ግን ምን እንደሚሆን የሚገልጽ ባለመሆኑ ካልተሰረዘ ጸንቶ እንዳለ የሚያመለክት በመሆኑ መ/ሰጪ የይ/ባይን ግመሎች ካለአግባብ የወረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ በመሆኑ መ/ሰጪ የግመሎቹን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በወቅቱ ዋጋ መሰረት ለይ/ባይ ይከፈል ሲል ወስኗል፡፡ መ/ሰጪ የአሁን አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 195827 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት ዲክላራሲዮን ጸንቶ ባለበትና ባልተሰረዘበት ሁኔታ ግመሎቹ ሊወረሱ አይገባም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 15 እና ከመመሪያ ቁጥር 118/2008 አንቀጽ 20 አኳያ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 22 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሚያዝያ 12 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ 43 ግመሎች ወደ ውጪ ለመላክ ህጋዊ መስፈርቶቹን አሟልቶ በአሁን አመልካች ፈቃድ ዲክላራሲዮን ተሰጥቷቸው በጉምሩክ ክልል የገቡና ወደ ውጪ ሳይላኩ የቆዩና ግመሎቹን ወደ ውጪ መላኪያ ጊዜ 5 የስራ ቀን ያለፈበትና ግመሎቹ በጉምሩክ ክልል ውስጥ የተገኙ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በህጋዊ መንገድ ወደ ውጪ የሚላኩ እቃውች በተፈቀደው ቀን ሳይላኩ በቀሩበት ጊዜ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክላራሲዮኑ ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማሳወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ 5 የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት ካልተጀመረ ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የመመሪያ ቁጥር 118/08 አንቀጽ 20(4 እና 5) ደግሞ እቃ ወደ ሀገር እንዲገባ ወይም እንዲወጣ ከተፈቀደ ጀምሮ በተለያየ ምክንያት ሳይፈጸም ከቀረ በ10 ቀናት ውስጥ ሲያሳውቅ ሊሰረዝ ይችላል ሲል ደንግገው ይገኛሉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ግመሎቹን በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጪ ሳይልካቸው 5 የስራ ቀን አልፎበታል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ዲክላራሲዮኑን አሰርዞ ግመሎቹን ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት የሚገባው ሲሆን ዲክላራሲዮኑ ካልተሰረዘ በዲክላራሲዮኑ መጠቀም ይችላል የሚል ትርጉም የሚሰጠው ሳይሆን ዲክላራሲዮኑን በማሰረዝ ሊያገኝ የነበረውን መብት የሚያጣ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ማለት ዲክላራሲዮኑ የመላኪያ ጊዜ ካለፈበት ግመሎቹን ከጉምሩክ ክልል አውጥቶ እንደገና ወደ ውጪ መላኪያ ማስፈቀጃ ዲክላራሲዮን የሚያወጣ አንጂ ጊዜ ባለፈበት ዲክላራሲዮን ወደ ውጪ መላክ የሚችል አይደለም፡፡ እንዲሁም የዚህ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 ድንጋጌ በህጋዊ መንገድ በጉምሩክ ክልል ውስጥ የገቡ ወደ ውጪ የሚላኩ እቃዎች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ውጪ ሳይላኩ የመላኪያ ጊዜው ያለፈበት አንደሆነ ላኪው ዲክላራሲዮኑን በማሰረዝ የሚሰጡትን መብቶች መጠቀም የሚችል ሲሆን ዲክላራሲዮኑን ካላሰረዘ ግን ውደ ውጪ ሊልካቸው በጉምሩክ ክልል ውስጥ የገቡት እቃዎች ህግ ወጥ ሆነው እንደ ኮንትሮባንድ እቃ ይወረሳሉ የሚል ትርጉም የሚያሰጠውም አይደለም፡፡ እቃ ወደ ውጪ ለመላክ በህጋዊ መንገድ በጉምሩክ ክልል የገባ እቃ የመላኪያ ጊዜው ካለፈበት ከጉምሩክ ክልል በማስወጣት ወደ መደበኛው ሁኔታ እንዲመለስ ከሚደረግ በቀር በህጋዊ መንገድ በጉምሩክ ክልል የገባ እቃ የመላኪያ ጊዜ ስላለፈበት ብቻ በህገ ወጥ መንገድ ወደ ወጪ ለማስወጣት የጉምሩክ ክልል ውስጥ እንደ ገባ እቃ እንደ ኮንትሮባንድ ተቆጥሮ የሚወረስ ስለመሆኑ የጉምሩክ አዋጁ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከዚሁ አንጻር አይቶ አሁን አመልካች ካለ አግባብ የወረሰውን የተጠሪ ግመሎች ለአሁን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ በወቅቱ በነበራቸው ዋጋ እንዲመለስ ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 195827 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 243070 ሐምሌ 3 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ/ቁጥር 289667 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም